**Ethiopian Journal of Business and Social Science**

**DOI:** *https://doi.org/10.59122/164F53bY*

**Volume: 7 Number: 1 , 2024 , Pages: 24~52**

**ISSN:2707-2770**

# ይዘት ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የ10ኛ ክፍል ተማሪዎችን አከራካሪ ድርሰት ከመጻፍ ክሂል አላባውያን ውስጥ ይዘትን እና የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት ላይ ያለው አስተዋፅዖ

**Ayalsew Yitayew**
*Email: ayalsewyitayew@gmail.com*

***Article Info***

*Accepted on:March, 2024*

*Published on: June, 2024*

***©Arba Minch University, all rights reserved***

***አጠቃሎ***

*የጥናቱ ዋና ዓላማ ይዘት ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ በአከራካሪ ድርሰት ከመጻፍ ክሂል አለባውያን ውስጥ ይዘትን እና ከተነሳሽነት መገለጫ ከሆኑት ውስጥ የግለ ብቃት የመጻፍ ተነሳሽነትን ማጎልበት ላይ ያለው አስተዋፅዖንን መመርመር ነው። የጥናቱ ንድፍ ባለሁለት ቡድን ሙከራዊ ነው። የጥናቱ ተሳታፊዎች በአዲስ አበባ መስተዳድር በዳግማዊ ምኒልክ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2014 ዓ.ም 10ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ከነበሩ 609 /ስድስት መቶ ዘጠኝ/ ተማሪዎች መካከል በእጽል ሰጪ ንሞና የተመረጡ የ10 ኛ - C ፣ የ10 ኛ- E እና የ10ኛ - H ክፍል ቡድኖችን ቅድመ የጽሁፍ ፈተና በመፈተን ተቀራራቢ ውጤት ያገኙትን የ10 ኛ - C እና የ10ኛ - E -ቡድኖች ለሙከራ እና ለቁጥጥር ቡድን ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርገዋል። ከእነሱም በፈተና፣ በጽሑፍ መጠይቅ እና በምልከታ አማካይነት የጥናቱ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በቅድመፈተና እና በቅድመ የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ ውጤቶች በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት (Independent samples t-test) ተተንትነዋል። በትንተናው የተገኙት ውጤቶች እንደ ሚያመለክቱት በቅድመ ፈተና እና በቅድመ የጽሑፍ መጠይቅ ተመጣጣኝ አማካይ ውጤቶች የተመዘገበባቸው ቡድኖች፣ በድኅረፈተና በመጻፍ ክሂል ውስጥ ካሉት አላባውያን ውስጥ ይዘት እና በድኅረ የጽሑፍ መጠይቅ ደግሞ ግለብቃትን የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ጉልህ የሆነ ልዩነት አሳይተዋል (P= <0.05)። ከዚህም በመነሳት ይዘት ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን በአከራካሪ ድርሰት የመጻፍ ክሂል አላባውያን ውስጥ ይዘትእና ከመጻፍ ተነሳሽነት ግለብቃትን ለማጎልበት ከተለመደው የማስተማር ዘዴ የበለጠ ውጤታማነት አለው ከሚል መደምደሚያ ላይ ተደርሷል። በጥናቱ ውጤት መሰረትም ይዘት ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን በአከራካሪ ድርሰት የመጻፍ ክሂል አለባውያን ውስጥ ይዘት እና ከመጻፍ ተነሳሽነት ግለብቃትን ለማጎልበት ያለው ውጤታማነት ጠቃሚ መሆኑ በመፍትሄነት ተጠቁሟል።*

***ቁልፍ ቃላት፣*** *ይዘት፣ አደረጃጀት፣ ተነሳሽነት፣ ግለብቃት፣የመጻፍ ክሂል ችሎታ ድርሰት*

**1. የጥናቱ ዳራ**

የመጻፍ ክሂልን ማስተማር ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካለንበት ዘመን ድረስ በርካታ የመጻፍ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎች በባለሙያዎች ተነድፈው አገልግሎት ሲሰጡ ቆይተዋል፡፡ የመጀመሪያው ውጤታዊ አቀራረብ ሲሆን ይህም፣ በአብዛኛው ጥንታዊ ወይም ልማዳዊ በመባል የሚጠቀሱትን የማስተማር ስነ ዘዴዎች የሚያካትት ነው፡፡መጻፍን በመማር ማስተማር የመጀመሪያው አቀራረብ ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ዘዴው በድርሰት ማስተማር ሂደት ውስጥ ብቸኛ የማስተማሪያ መንገድ ሆኖ አገልግሏል፡፡ አቀራረቡ ለቋንቋ ቅርጽ(form) ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥ ሲሆን፣ መጻፍን የሚመዝነው በጽሁፍ ውስጥ የሰዋስዋዊ ህግጋት ተስተካክለው መጻፋቸው ላይ ነው፡፡

ይህ አቀራረብ ተማሪዎች ለሚጽፏቸው ጽሁፎች ምሳሌ ይሆናሉ፡: ጥሩ ተጽፈዋል ተብለው የሚታሰቡ ጽሁፎችን አቅርቦ ሰዋስዋዊ ህጎችን፣ አደረጃጀትን፣ የአጻጻፍ ስልትን፣ ወዘተ. ተንትኖ ማሳየትና ተማሪዎች የተመለከቱትን በጽሁፋቸው እንዲያሳዩ የማድረግ ቴክኒክንም ይተቀማል (Leki,.1996; Pinka, 1986)፡፡ ሆኖም ይህ የማስተማሪያ መንገድ በድርሰት አዘገጃጀት ሂደት ላይ ትኩረት አያደርግም፡፡ ትኩረቱ ትክክለኛ ድርሰት ወይም ውጤት ከማግኘት ላይ ነው፡፡ ውጤታዊ አቀራረብ የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር ለረጅም ጊዜ ብቸኛ የማስተማሪያ ስልት ሆኖ ሲገለግል የቆየ ቢሆንም በሂደት በደካማ ባህርያቱ ሊተችና የትኩረት አቅጣጫውም በሌላ የመጻፍ ክሂል የማስተማሪያ ዘዴ ሊተካ ችሏል፡፡

ሁለተኛው፣ ሂደታዊ አቀራረብ ሲሆን ትኩረት የሚያደርገው በጸሀፊው ላይ ነው፡፡ አቀራረቡ ከመነሻው የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንግሊዝኛ የሆኑ ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማስተማር ታቅዶ የተጀመረ ነው፡፡ በኋላ ግን እንግሊዝኛን እንደሁለተኛ እና እንደውጪ ቋንቋ በሚማሩ ተማሪዎች የአጻጻፍ ስትራቴጂ ላይ በተካሄዱ ምርምሮች ከአፍ ፈቶች ጋር ተመሳሳይ ሂደት ያለው ሆኖ በመገኘቱ ለኢአፈ ፈቶች ማስተማሪያነት ሊውል ችሏል (Korol, 1991; Raimes, 1985; Zamel, 1993)

የዚህ አቀራረብ መለያ ባህርያትም ጸሀፊው በመጻፍ ሂደቱ ወቅት የሚከናውናቸው ተግባራት መኖራቸው ነው፡፡ Raimes (1991) እንደሚያብራሩት በዚህ አቀራረብ ከፍተኛ ግምት የተሰጠው ለትክክለኛነት (acuracy) እና ለቅርፆች (patternes) ሳይሆን ለአጻጻፍ ሂደት ነው፡፡ በመጻፍ ትምህርት ላይ አጽንኦት የሚሰጡ ወገኖች በቅርብ ዓመታት ውስጥ ትኩረታቸውን ከውጤታዊ አቀራረብ ወደ ሂደታዊ አቀራረብ ቀይረዋል (Raimes, 1911)፡፡

ሂደታዊ አቀራረብ ተጽፎ በተጠናቀቀ ድርሰት ላይ ሳይሆን ደርሰት በመጻፍ ሂደት ላይ ስለሚያተኩር ጸሀፊዎች በአብዛኛው ራሳቸውን የሚጠይቁት ስለ ድርሰት ዓላማና ስለ አንባብያኑ (audience) ሳይሆን ድርሰቱን እንዴት ልጀምረው እንዴትስ ልጻፈው በሚሉት ነጥቦች ላይ ነው (Me carthey & Ro, 2011; Raimes, 1911)።

ሦስተኛው ዘውግ ተኮር አቀራረብ ደግሞ፣ በሁለተኛ ቋንቋ ላይ በመጻፍ ክሂል ዙሪያ ጥናትና ምርምሮች ማካሄድ የጀመሩት በ1960 ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ሲሆን፣ አብዛኞቹ ጥናቶችም ትኩረት ያደረጉት በመጻፍ ማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ ነበር። ይህም ጥረት ተማሪዎቹ በርካታ ደረጃዎቹን አልፈው ድርሰት ወደ ሚጽፉበት ወደ ሂደታዊ አቀራረብ ፣ በመቀጠልም ለአንድ ለተለየ ዓላማ የሚጻፍ ጽሁፍ ስለሚኖረው ቁልፍ መለያ ባህሪና በሞዴል ላይ ትኩረት የሚያደርገው ዘውግ ተኮር አቀራረብ ብቅ ሊል ችሏል ( Kim ,n.d )።

ዘውግ ተኮር አቀራረብ በአንድ ጉዳይ ላይ ያጠነጠኑ የጽሁፍ ናሙናዎችን ለተማሪዎች በማስተዋወቅ ፣ የናሙናውን ልዩ ባህሪ ነቅሶ በማውጣት ተማሪዎቹን የዘውጉን መለያ ባህሪ በመጻፍ ቀደም ሲል የቀረበውን ናሙና አስመስለው ረቂቅ እንዲያዘጋጁ የሚደረግበት የማስተማሪያ መንገድ ነው (Elshirbini, 2013; Oraife, 2016)። በዘውግ ተኮር አቀራረብ ብዙ ጊዜ መጻፍ የሚታሰበው፣ መምህሩ አስቀድሞ በሚያስቀምጠው ዘውግ መሰረት ተማሪው ቴክስት የሚያዘጋጅ ሲሆን ሂደታዊ አቀራረብ ግን ትኩረት የሚያደርገው በጸሀፊው ላይ ነው፡ ፡ ይህ ዓይነቱ አቀራረብ የራሱ የሆነ ደካማ እና ጠንካራ ጎኖች ቢኖሩትም ተማሪዎቹን መጻፍ ክሂል በማጎልበት ረገድ ከሂደታዊ አቀራረብ የተሸለ እንደሆነ Elshirbini (2013) ዋቢ ያደረጓቸው (Burns 2001, Ding Eng Na, 2009; Tangmermepoon,2008,) ያስረዳሉ።

በአጠቃላይ የመጻፍ ትምህርት አቀራረቦችን ስንመለከት ከውጤታዊ አቀራረብ ድክመት በመነሳት ሂደታዊ አቀራረብ እንዲሁም ከሂደታዊ አቀራረብ ድክመት በመነሳት ዘውግ ተኮር አቀራረብ እየተተካኩ ቀርበዋል። በመሆኑም ለተማሪዎች ከሚቀርብላቸው የመጻፍ ችሎታቸውን ሊያጎለብትላቸው የሚችለውን ተግባቦታዊ ቋንቋ የማስተማሪያ ዘዴ በመመርመር ማሳየት የሚቻልበትን አቅጣጫ መጠቆም ወሳኝ ነው። ከእነዚህም ተግባቦታዊ ቋንቋ ማስተማር ላይ ከተመሰረቱ የማስተማሪያ ዘዴዎች መካከል አንዱ ደግሞ ይዘት ተኮርየ ቋንቋ ማስተማርያ ዘዴ ነው።

የቋንቋክ ሂልን በማስተማርያነት ከሚያገለግሉት ዘዴዎች መካከል የሚጠቀሰውና የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነውና አማራጭ ዘዴ ሆኖ የሚቀርበው ደግሞ የይዘት ተኮር ቋንቋን የማስተማርያ ዘዴ ነው። Finkbeiner

and Fehling (2002) ሲገልጹ ይዘት ተኮር ቋንቋን የማስተማርያ ዘዴ ሂደታዊ መርሀት ምህርትን መሰረት በማድረግ የሚሰራበት ነው። ምሁራኑ በመጻፍ ትምህርት አቀራረቦቹን ዓላማና ተግባር በግልጽ ያስረዱ ቢሆንም በመማር ማስተማሩ ሂደት የተሻለውን የማስተማርያ ምርጫ ለማወቅ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ይዘት ተኮር ቋንቋን የማስተማርያ ዘዴ፣የተግባቦታዊ የቋንቋ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ ሁለት ማጠንጠኛ መርሆዎች እና መነሻ ሀሳቦች እንዳሉት Stryker and Leaver (1993) Richards and Rodgers (2001) የሚከተሉትን ነጥቦች ይገልፃሉ። ይኸውም፣አንደኛው ተማሪዎችን አንድን ሁለተኛ ቋንቋ ስናስተምር፣ ትምህርታዊ መረጃ እንዲያገኙበት አድርገን ብናስተምራቸው የበለጠ ውጤታማ ይሆናሉ የሚልሲ ሆን፣ ሌላኛው ይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪ ያዘዴ ቋንቋን ለመማር የተማሪዎችን ተነሳሽነት (ፍላጎት) መሠረት ያደረገ የማስተማሪያ ዘዴነው።

የመጻፍ ተነሳሽነት የሚያመለክተው የተማሪዎችን ዝንባሌ፣ ዕውቀት እና የመፃፍ ፍላጎትንነ ው።ድርሰቶችን፣ ታሪኮችን፣አጫጭር መልሶችን እና ሪፖርቶችን ጨምሮ አብዛኛው የፅሁፍ ተነሳሽነት እና የተሳትፎ ምርምር በግላዊ ተነሳሽነት እና ተሳትፎ ላይ ያተኮረ ነው- ለምሳሌ፣ በራስ መተማመን ማጣት፣የተማሪዎች ፍርሃት እና ጭንቀት የመነሳሳት እና የተሳትፎ ሁኔታዎችን ይገድባል። በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተነሳሽነት የሚለው ስነልቦናዊ ጽንሰሀሳብ ሲታሰብ በውስጡ ተያይዘው የሚነሱ ሌሎች ስነልቦናዊ ጽንሰሀሳቦች አሉ። Pajares and Johnson (1996), Pajares and Valiente (1997) Payne (2012) Zimmerman and Bandura (1994) እንደሚገልጹት ግለብቃት፣ ግለግንዛቤ እና ግለመር ከተነሳሽነት ጋር ሊያያዙ የሚችሉ መገለጫዎች እንደሆኑ ያስረዳሉ። በመሆኑም በዚህ ጥናት ርዕስ ስር ትኩረት ከሚደረግባቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች ውስጥ በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ ድርሰት የመጻፍ ክሂል አለባውያን ውስጥ ይዘትን እና በመጻፍ ተነሳሽነት መገለጫ ከሆኑት ውስጥ ደግሞ ግለ ብቃትን መመርመር ነው።

የመጻፍ ግለብቃት ተነሳሽነትን አስመልክተው Hashemenejad et al. (2014) ከመጻፍ ትምህርት ጋር አያይዘው የግለ ብቃት ምንነትን እንደሚያስረዱት፣ ተማሪዎች ከመጻፍ ችሎታቸው ጋር በተያያዘ አለኝ ብለው የሚያምኑት አቅም/ብቃት ነው።ግለብቃት ብዙውን ጊዜ ከተማሪዎች የመጻፍ አፈጻጸም ውጤቶች ጋር ተቆራኝቷል። በግንዛቤ ውጤታማ ጎራ ውስጥ ካሉ ከማንኛውም ሌሎች አካላት በበለጠ፣በራስ የመተማመን እምነት በጽሁፍ የአፈጻጸም ውጤቶች መተንበይን ያረጋግጣል።በአጠቃላይ ግለብቃት አንዱ የተነሳሽነት ገጽታ

ሲሆን፣ ተማሪዎች ቀደም ሲል ካከናወኗቸው ልዩልዩ የመጻፍ ተግባራት ተነስተው፣በሂደት ከሚያሻሽሉት የመጻፍ ችሎታ አንጻር አለኝ ብለው ሊገልጹት የሚችሉት አቅም/ብቃት ነው፡፡ ሌላው ትኩረት ከሚደረግባቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች ውስጥ ደግሞ በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማርያ ዘዴ መማር በአከራካሪ ድርሰት የመጻፍ ክሂል አለባውያን ውስጥ ይዘት ላይ ያለውን አስተዋፅዖ መመርመር ይሆናል፡፡

ክርክራዊ ድርሰትን አስመልክተው Holman, William (2003) አመዛዛኝ/ አከራካሪ ጽሑፍ በአንድ ጉዳይ ላይ አቋም የሚወስድ የጽሑፍ ክፍል ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡ እንዲሁም Hairston, (1981) አከራካሪ ድርሰት አከራካሪ ስለሆኑጉዳዮች የሚጽፍ፣አንባቢውን የአንድን ጉዳይ እውነትነት ወይም ሐሰትነት ለማሳመን የሚጥር ደራሲው /ጸሀፊው ለአንድ ወገን ቆሞ አንድን ጉዳይ በአንድ መልኩ ብቻ በመቃወም አቅርቦ በመጨረሻም ማስረጃው ያደላበትን አጠናክሮ በመተቸት አንዱን በማጠናከር ወደ አንድ ውሳኔ የሚደርስበትና ለማሳመን የሚጥርበት የድርሰት ዓይነት ነው፡፡በተጨማሪም Fahnestock (2000) የሃሪስቶንን ሀሳብ ሲያጠናክሩ፣ ሰዎች ሁልጊዜ ትክክል ወይም ምክንያታዊ በሆነ ነገር ላይ ስለማይስማሙ፣ በተገቢው መንገድ የተገነባ ክርክር ትክክለኛ ወይም እውነት ላይ እንድንደርስ ይረዳናል። በመሆኑም ተማሪዎች በይዘት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ በመመርኮዝ በሚጽፉት አከራካሪ ድርሰት፣ ግጭቶችን ለመፍታት እና እውነትን ለማወቅ ይችላሉ።ተማሪዎች የራሳቸውን እና የሌላውን ሀሳብ በጥንቃቄ፣ ስልታዊ በሆነ መንገድ በመመርመር እንዲማሩ እድል ይሰጣል። አከራካሪ ድርሰት እርስ በእርሱ የሚጋጭ፣የይሻላል ጥያቄዎችን እንዴት መገምገም እና ማስረጃዎችን እና የምርመራ ዘዴዎችን መፍረድ እንደሚቻል ያስተምራል።

በይዘት ተኮር ዘዴ ላይ የተመሠረቱ የንድፈ-ሀሳብ መሠረቶች ከሆኑት ውስጥ የይዘት ተኮር ቋንቋ የማስተማሪያ ሞዴሎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ሞዴሎች በተመረጡ አርእስቶች ወይም ጭብጦች ዙሪያ የቋንቋ ሥርዓተ-ትምህርትንበማዘጋጀት በመሰረታዊ ቋንቋ ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡የቋንቋ መማሪያ ቁሳቁሶች በመምህሩ የሚዘጋጁ ወይም ከውጭ ምንጮች የሚመጡ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ብዙውን ጊዜ ርዕሱን ከሁሉም ሙያዎች ጋር ማስተማር እና ለማቀናጀት ሙከራ ይደረጋል (Brinton et al., 1989)፡፡በዚህም መሠረት በባለሞያዎች ሊተገብሯቸው የሚችሉ ሦስት የይዘት ተኮር ቋንቋ የማስተማሪያ ዘዴ ሞዴሎችን ይጠቅሳሉ:: እነዚህም፡-ጥልል ሞዴል / Sheltered Model/፣ተጨማሪ ሞዴል/Adjunct Model/፣የጭብጥ ተኮር ሞዴል / Theme Based Model / ናቸው፡፡

የመጀመሪያው ጥልልሞዴል /Sheltered Model/ ሲሆን መምህራን በልዩ የቋንቋ ትምህርት ተማሪዎቻቸውን ማብቃት በሚችሉበት ተቋም ውስጥ የሚያገለግል ሲሆን፣ ከመደበኛ አፈ-ፈት ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ ይዘት ለማጥናት ያስችላል። ምክንያቱም ተማሪዎች መደበኛ ትምህርቶችን ለመረዳት እንዲረዳቸው ልዩ ድጋፍ ሲፈልጉ የተማሪዎችንየቋንቋትምህርትውስንብቃት በማስተካከል የይዘትሥርዓተ-ትምህርትንይጠቀማል። በማለት Brinton et al. (1989) ይገልጻሉ ።

ሁለተኛው ደግሞ ተጨማሪ ሞዴል /Adjunct Model/ የሞዴሉ ትምህርት ዓላማ ተማሪዎችን ማዘጋጀት ነው። በዚህ ሞዴል ውስጥ ተማሪዎች ሁለት የተያያዙ ትምህርቶችን በተጨማሪ ያሳያሉ ይኸውም፡- የይዘት ትምህርት እና የቋንቋ ትምህርት ሲሆኑ ሁለቱም ትምህርቶች አንድ ዓይነት ይዘት ቢኖራቸውም በትምህርታቸው ትኩረት ግን ይለያያሉ። የቋንቋ መምህራን የቋንቋ ችሎታዎችን አፅንዖት ይሰጣሉ:: ከዚህ ሞዴል በስተጀርባ ያለው መሰረታዊ ምክንያት ተማሪዎች ከአንድ ተግባር ወደሌላ ተግባር የሚሸጋገሩ የአካዳሚክ የመቋቋም ስልቶች እና የእውቀት (ኮግኒቲቭ) ክህሎቶች እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል የሚል ነው (Brinton, 2003; Richards & Rodgers, 2001)።

ሌላው በሶስተኛነት የተጠቀሰው የጭብጥ ተኮር ሞዴል / Theme Based Model / ሲሆን በዚህ ሞዴል ሥርዓተ ትምህርቱ ይዘጋጃል። በጭብጦች ወይም በርዕሶች ዙሪያ ላይ ያተኩራል። በይዘት ተኮር ትምህርት አቀራረብ ገጽታውን ለማስተዋወቅ የተለያዩ መንገዶች አሉ። ለምሳሌ ቪዲዮ እና የድምጽ ቁሳቁስ፣ ንባብ / ወይም የቃል ቃላት ይጠቀማል። እነዚህን ገጽታዎች ወይም ርዕሶችን ለማስተዋወቅ ያገለግላል። በእነዚህ ትምህርቶች ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ጭብጦች ብዙውን ጊዜ በጣም አስፈላጊ ትምህርቶችን ይሰጣሉ። በዚህም ብዙ ጠቃሚ ግብዓቶች ይገኛሉ እንዲሁም ታላሚውን ቋንቋ በተሳካ ሁኔታ ለማግኘት እነዚህ ገጽታዎች በጭብ ጥተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ውስጥ ዋና ሚና ይጫወታሉ (Brinton, 2003; Richards & Rodgers, 2001; Stryker & Leaver, 1993)።

በጭብጥ-ተኮር የቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከሥርዓተ-ትምህርቱ በተውጣጡ በተመረጡ ርዕሶች ወይም ጭብጦች ዙሪያ የቋንቋ ሥርዓተ-ትምህርት ይዘጋጃል። በይዘት-ተኮር የቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያሉ ቁሳቁሶች አብዛኛውን ጊዜ በአስተማሪ የሚዘጋጁ ወይም ከውጭ ምንጮች የሚገኙ ናቸው።ርዕሰ ጉዳዩን ከሁሉም ክህሎቶች ማስተማር ጋር ለማቀናጀት ብዙውን ጊዜ ሙከራ ይደረጋል።ዓላማው አስደሳች እና አግባብነት ባለው

ይዘት አጠቃላይ የአካዳሚክ ቋንቋ ችሎታዎችን እንዲያዳብሩ መርዳት ነው። ጭብጥ-ተኮር የቋንቋ ትምህርት ከሦስቱም ይዘት-ተኮር ሞዴሎች እጅግ በጣም የተስፋፋ ነው፣ምክንያቱም በማንኛውም ነባር ተቋማዊ አሠራር ውስጥ ሊተገበር ስለሚችል፣ጭብጡ ወይም ርዕሱ ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር የሚስማማ ሆኖ ሊመረጥ ይችላል (Brinton et al.,1989)::

እንደዚሁም Brinton et al.,1989 እንደሚያመለክቱት በጭብጥ ላይ የተመሰረቱ ትምህርቶች በአንፃራዊነት ውስብስብነት አይታይባቸውም። በይዘት ተኮር ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ውስጥ ጭብጥ ተኮር ሞዴል በጣም የተለመደ ነው። በርዕሰ-ተኮር ሞዴል ውስጥ የተመረጡ ርዕሶች ወይም ጭብጦች ተማሪዎች እንዲማሩበት ይዘቱን ያሳያሉ።ዋና ዋና የሥርዓተ ትምህርት ክፍሎችን የሚያደራጁ ማዕከላዊ ሀሳቦች ናቸው፣ ስለሆነም ለተማሪዎች የትምህርት እና የእውቀት (ኮግኒቲቭ) ፍላጎቶች ተስማሚ እንዲሆኑ መመረጥ አለባቸው። በተጨማሪም፣ በርዕሰ-ተኮር የቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያሉ ቁሳቁሶች አብዛኛውን ጊዜ በአስተማሪው የሚመነጩ ወይም ከውጭ ምንጮች የሚመጡ ናቸው።

ይህንኑ ሀሳብ Grabe and Stoller (1997) ሲያጠናክሩ ጭብጥ-ተኮር መመሪያ ለቋንቋ ሥርዓተ-ትምህርት ንድፍ ባህላዊ አቀራረቦች የጎደለውን ልኬት ይጨምራል።በእውነተኛ ተግባቦት ላይ ሳይሆን በቅጽ ላይ እና በእውቀት ላይ የተመሠረተ /ተግባራዊ ሥርዓተ ትምህርት በሕጎች ላይ የሚያተኩርበት፣የቋንቋ ትምህርቶችን ለተማሪዎች ለመማር ወይም ለመግባባት አስደሳች ርዕሰ-ጉዳይ ይሰጣል፤ የቋንቋ ይዘትን ለመመርመር ጥቅም ላይ ይውላል፤ በመሆኑም ተማሪዎች ከይዘት ጋር የሚዛመድ ቋንቋን በመረዳታቸው የቋንቋ ክሂላቸውን ያሻሽላሉ።

ከላይ ከተዘረዘሩት በይዘት ላይ ከተመሰረቱ ሞዴሎች ውስጥ ይህ ጥናት የተከተለው በጭብጥ ላይ የተመሰረተውን ሞዴል ነው። ይህ ሞዴል በዚህ ጥናት ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል የተደረገበት ምክንያት፣ ጭብጥ ላይ የተመሠረተ የይዘት ተኮር ትምህርት በተለየ ምክንያት መምህራን ተማሪዎቻቸው እንዲደሰቱ የሚሰማቸውን ማንኛውንም የይዘት ቁሳቁሶች መጠቀም ይችላሉ። እንዲሁም፣ ትክክለኛ ቁሳቁሶች ርዕሰጉ ዳዩን ከሁሉም የቋንቋ ችሎዎች ትምህርት ጋር ለማቀላቀል በመሞከር ከፍተኛ ምርጫናቸው። በተጨማሪም የተማሪዎችን ተነሳሽነት እና ፍላጎት ማሳደግ በይዘት ላይ የተመሠረተ መመሪያን መሠረት ያደረጉ ሁለት አስፈላጊ ነገሮች ናቸው ይላሉ። እነዚህም- ስኬታማነትን የሚደግፉ እና የተማሪዎችን ውስብስብ ክህሎቶችን

እንዲማሩ የሚያግዙ፣ፈታኝ በሆኑ መረጃ ሰጭ ተግባራት የተማሪዎችን ስኬት ለመደገፍ ተነሳሽነት እና ፍላጎት ወሳኝ ናቸው (Brinton et al.,1989; Grabe & Stoller,1997)።

ይዘት ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ ሥራ ላይ ማዋል ከጀመረ ጊዜ አንስቶ የተለያዩ ተመራማሪዎች ለቋንቋ ትምህርት ያለውን ሚና በተመለከተ ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል። እንደ Lyster & Ballinger (2011) አገላለጽ ይዘት ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ በቋንቋ ክሂሎች የትምህርት አቀራረብ ላይ መተግበር መቻሉ እንደ ጠንካራ ጎን ሊነሳ የሚችል ነው። ለዚህ ደግሞ ማሳያ ሊሆን የሚችለው ዘዴው ከማንበብ፣ ከመጻፍ፣ ከንግግር እና ከማዳመጥ አንጻር ያለውን ሚና በሚመለከት የተደረጉ ጥናቶች መኖራቸውና በዘዴው ላይ አወንታዊ እና አሉታዊ ጎኖችን ማሳየት መቻላቸው ነው።

ይዘት ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴን አስመልክተው Richards and Rodgers (2001) ሲገልጹ፣ ቋንቋ እና ይዘትን በውህደት የሚያስተምር ዘዴ ነው።ዘዴውም የተማሪዎችን ፍላጎት እና ዳራዊ ልምዳቸውን መሰረት በማድረግ አዲሱን መረጃ እንዲማሩት የሚያደርግ ሲሆን፣በይዘት ተኮር ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴ ቋንቋን በምናስተምርበት ወቅት ተማሪዎች ትኩረት የሚያደርጉት በቋንቋው ላይ ሳይሆን ከሚማሩት ይዘት ወይም ጭብጥ ላይ ነው፤ በመሆኑም በዚህ ዘዴ ቋንቋን መማር እንደተጨማሪ ውጤት (by product) የሚታይ ነው ማለት ይቻላል።

Lyster & Ballinger (2011) በጥናታቸው ትምህርት የበለጠ ተዘማጅ እና እውቀት የሚጠይቅ በመሆኑ፣ይዘትን እና ቋንቋን ማዋሃድ ለቋንቋ ተማሪዎች ብዙ ጥቅሞች እንዳሉት ሲገልጹ፣በይዘት ተኮር ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴ ክፍሎች ውስጥ መስተጋብሮች ትርጉም ያላቸው በመሆናቸው ተማሪዎች መደበኛ እና መደበኛ ያልሆነ፣ አጠቃላይ ትምህርትን ጨምሮ በተለያዩ ጎራዎች ውስጥ የተግባቦት ችሎታዎችን እንዲያዳብሩ ያደርጋል፤ ይህም የተማሪን ተነሳሽነት እንዲጨምር እድል ይከፍታል፤ትኩረቱን ለይዘትና ቋንቋ በመስጠቱ፣ ከተለምዷዊ /ከነባሩ ቋንቋን የማስተማሪያ ክፍሎች ከፍያ ለየብቃት ደረጃዎችን ለማሳካት ያስችላል።

ነገር ግን ይዘት ተኮር ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴ ለቋንቋ ክሂሎች መጎልበት አስተዋፅኦ እንዳለው በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ቢገልጹም፣ እንዲሁም ደግሞ በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ ላይ የሚነሱ ትችቶች አሉ። ከእነዚህ ትችቶች ውስጥም፣ ዘዴው ሲተገበርለተማሪዎችምሆነለአስተማሪዎችየተለያዩተግዳሮቶች መኖሩን ያስረዳሉ። ከነዚህም ውስጥ Lyster and Ballinger (2011)፣ Cammarata and Tedick, (2012) ለተማሪዎች

በትምህርቱ ቋንቋ ውስጥ ብቃት ምክንያት የአካዳሚክ ፅንሰ -ሀሳቦችን እና ክህሎቶችን ማወቅ ይኖርባቸዋል በማለት ይገልጻሉ፡፡ መምህራን የይዘት ተኮር ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር ይቸገራሉ፤ እናም በተለያዩ ምክንያቶችየ ይዘት ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ መምህራን ብዙውን ጊዜ በክፍል ውስጥ እንደቋንቋ ባለሞያ ሆነው ለመሥራት በቂ ብቃት አይሰማቸውም፣ የቋንቋ መምህራን በሚሸፍኑት የይዘት ክፍል ውስጥ ሁልጊዜ በራሳቸው ዕውቀት ላይ እርግጠኛ አይደሉም (Lyster & Ballinger, 2011)፡፡ እንዲሁም፣ Stryker and Leaver (1993) ይህንኑ ሀሳብ ሲያጠናክሩ፣ ይዘት ተኮር ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴ የተሻለ የቋንቋ መምህራንን ይፈልጋል። የቋንቋ መምህራን በይዘት አካባቢዎች ዕውቀት ያላቸው እና ለተማሪዎች ዕውቀትን ማስገኘት መቻል አለባቸው።

ከነዚህ ምሁራን ሃሳብ በተጨማሪ በይዘት ተኮር ዘዴ መማር የተማሪዎችን አቅምና የትምህርት ውጤት በማጎልበት ሂደት ውስጥ የሚጫወተውን ሚና ምሁራን በተለያየ ጊዜ ባሳተሟቸው የምርምር ስራዎች ላይ አስፍረዋል፡፡ ለምሳሌ፡- Dueñas (2004)፣ Grabe and Stoller (1997) ያካሄዱት ጥናት የሚጠቀስ ሲሆን፣ በዚህ ጥናት ውስጥ በይዘት ተኮር ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴ፣ተማሪዎች ሰፊ የብቃት ደረጃ-ተኮር፣ ትርጉም ያለው እና ተዛማጅ ግብዓትን ይቀበላሉ በተመሳሳይ ጊዜ ትርጉም ባለው ተግባቦት ውስጥ ለመሳተፍ ብዙ እድሎች አሏቸው።በተለያዩ ዓይነት ሞዴሎች ውስጥ በተካሄዱት መርሀግብር ውጤቶች ላይ የተደረገው ጥናት፣ይዘት ተኮር ቋንቋን የማስተማርያ ዘዴ በቋንቋ እና በይዘት ትምህርት ውስጥ ውጤት አስገኝቷል፤ ተነሳሽነትን ፈጥሯል እና ለሰዋስው ትምህርት ምቹ ሁኔታዎችንም ያዘጋጃል።በተመሳሳይ ሁኔታ፣ Richards and Rodgers (2001) መምህራን በይዘት ላይ የተመሠረተውን የቋንቋ ትምህርት ተማሪዎችን በአካዳሚክ ይዘት የሚያስተምሩበት ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴ መሆኑን እንዲሁም በተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ላይ አወንታዊ ሚና መፍጠር እንደተቻለ በጥናታቸው ውስጥ ገልጸዋል፡፡

ከላይ ሃሳባቸውን ካሰፈሩት ምሁራን ሃሳብ መረዳት የሚቻለው የይዘት ተኮር የማስተማርያ ዘዴ የተማሪዎቹን የመጻፍ ክሂል ችሎታን የሚያጎለብት፣ የተማሪዎችን ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ፣ የተማሪዎችን የመጻፍ ፍላጎት የሚጨምር፣ በራስ የመማር ችሎታን የሚያጎለብት፣ በራሳቸው የሚተማመኑ ወይም ችግር ፈቺ እና በመምህሩ ላይ ጥገኛ ያልሆኑ ተማሪዎችን መፍጠር የሚያስችል መሆኑን ነው፡፡

ይህ ጥናት ይዘት ተኮር ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴ በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አውድ ከአከራካሪ ድርሰት የመጻፍ ክሂል አለባውያን ውስጥ ይዘትን ለማጎልበት ያለው አስተዋፅኦ ላይ የሚያጠና ከመሆኑ ባሻገር የተነሳሽነት መገለጫ ከሆኑት ውስጥ ግለ ብቃትን፣ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታቸውን እና ከትምህርቱ አሰጣጡ ጋር አዛምዶ ማጥናቱ ወደፊት በክሂሉ መማር ማስተማር ላይ የራሱን አስተዋፅኦ ያደርጋል ብሎ አጥኝው ያምናል።

## 2. የጥናቱ ዋና ዓላማ

የጥናቱ ዋና ዓላማ ይዘት ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ በአከራካሪ ድርሰት የመጻፍ ክሂል አለባውያን ውስጥ ይዘትን እና በመጻፍ ተነሳሽነት ግለ ብቃትን ለማጎልበት፣ ያለው ውጤታማነት መመርመር ነው።

ዝርዝር ዓላማዎችም፡-

- ይዘት ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን አከራካሪ ድርሰት የመጻፍ ክሂል አለባውያን ውስጥ ይዘትን ለማጎልበት ያለው አስተዋፅዖ ምን እንደሚመስል ማየት፣
- በይዘት ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ የመጻፍ ክሂልን መማር በተማሪዎች የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት ያለው አስተዋፅዖ ምን እንደሚመስል ማየት፣የሚሉት ናቸው።

## 3. የጥናቱ መነሻ ችግር

ከመጻፍ ክሂል ጋር በተያያዘ በርካታ ጥናቶች ተካሂደዋል፤ እየተካሄዱም ይገኛሉ። መጻፍ፣የአፍልቆት ክሂል እንደመሆኑ መጠን ተማሪዎች ሀሳባቸውን፣ ስሜታቸውን፣ ፍላጎታቸውን፣ ወዘተ. እንዲገልጹ እና ልዩ ልዩ ልምምዶችን እንዲያከናውኑ የሚጠይቅ ክሂል ሲሆን፣ ክሂሉን ለማሻሻል ብዙ ጥረትን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ይህም የሆነበት ምክንያት ተማሪዎቹ በክሂሉ ውስጥ ያሉትን አላባውያን (ይዘት፣አደረጃጀት፣ቃላት፣የቋንቋ አጠቃቀም እና ሥርዓተ አጻጻፍን) በተግባር መለማመድ ስላለባቸው ነው (Nunan 1991; Ariningsih, 2010) ።

በዚህ ርዕስ ጥናት ለማካሄድ ከተፈለገባቸው ምክንያቶች አከራካሪ ድርሰት የመጻፍ ክሂል ችሎታ ከሌሎች ክሂሎች በበለጠ (በ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ) ትኩረት የተሰጠው በመሆኑ ፣ እንዲሁም ግርማኃይሉ (2009)፣ ሰሎሞን (1997)፣ ክፍሌ (1989)፣አማረ (2010)፣የሻረግ(2010)፣ኤፍሬም(2010)፣ Alamirew (2005) እንደገለጹት የመጻፍ ክሂል ችሎታ መጎልበት ለሌሎች ክሂሎች መጎልበት ዋነኛ ጉዳይ በመሆኑ ይህንን ትኩረት የተሰጠው አብይ ችሎታ በይዘት ተኮር የመማር ዘዴ ተግባራዊ በማድረግ በተማሪዎች ክርክራዊ ድርሰት

የመጻፍ ክሂል ችሎታና  በግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት ላይ የሚታውን ለውጥ በጥናት ለማረጋገጥ መፈለግ በዋናነት የሚጠቀስ ነው፡፡

በተጨማሪም በብዙ አጥኚዎች የተለያዩ ጥናት መቅረባቸው ማለትም አንዳንድ አጥኚዎች በይዘት ተኮር ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ መማር  ከትምህርት ውጤት ጋር ትስስር አለው የሚል የጥናት ውጤት ሲያቀርቡ ለምሳሌ፡- Lyster & Ballinger (2011)  አገላለጽ ይዘት ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ  ዘዴ በቋንቋ ክሂሎች የትምህርት አቀራረብ ላይ መተግበር መቻሉ እንደ ጠንካራ ጎን ሊነሳ የሚችል ነው፡፡ ይኸውም- በዘዴው ላይ አወንታዊ ጎኖችን ማሳየት መቻሉ ነው፡፡ Richards and Rodgers (2001) ሲገልጹ፣ ቋንቋ እና ይዘትን በውህደት የሚያስተምር ዘዴ ነው፡፡ዘዴውም የተማሪዎችን ፍላጎት እና ዳራዊ ልምዳቸውን መሰረት በማድረግ አዲሱን መረጃ እንዲማሩት የሚያደርግ ሲሆን፣ በይዘት ተኮር ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴ በሚማሩበት ወቅት ተማሪዎች ትኩረት የሚያደርጉት በቋንቋው ላይ ሳይሆን ከሚማሩት ይዘት ወይም ጭብጥ ላይ ነው፤ በመሆኑም በዚህ ዘዴ ቋንቋን መማር እንደተጨማሪ ውጤት (by product) የሚታይ ነው ማለት ይቻላል፡፡ Stryker and Leaver (1993) ተማሪዎች በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ ውስጥ በራሳቸው የሚተማመኑ ወይም ችግር ፈቺ እና በመምህሩ ላይ ጥገኛ ያልሆኑ እንዲሆኑ መላምት ይቀርባል፡፡ በመሆኑም የራሳቸውን የመማር ሂደት ያወቁ ተማሪዎች ለዚህ አዲስ የቋንቋ ትምህርት ዘዴ ፍላጎት ያድርባቸዋል፡፡  በመሆኑም ይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ መማር  ከትምህርት ውጤት ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ (አዎንታዊ ግንኙነት) እንዳለው ያስገነዝባሉ፡፡

መምህራን የይዘት ተኮር ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር እንደሚቸገሩ የገለጹት ደግሞ  Lyster & Ballinger (2011) በተለያዩ ምክንያቶች ሲሆን ይኸውም-የይዘት ተኮር መምህራን ብዙውን ጊዜ በክፍል ውስጥ እንደቋንቋ ባለሞያ ሆነው ለመሥራት በቂ ብቃት አይሰማቸውም፣ የቋንቋ መምህራን በሚሸፍኑት የይዘት ክፍል ውስጥ ሁልጊዜ በራሳቸው ዕውቀት ላይ እርግጠኛ አይደሉም፡፡ እንዲሁም፣ Stryker & Leaver (1993) ይህንኑ ሀሳብ ሲያጠናክሩ፣ ይዘት ተኮር ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴ የተሻለ የቋንቋ መምህራንን ይፈልጋል፡፡ የቋንቋ መምህራን በይዘት አካባቢዎች ዕውቀት ያላቸው እና ለተማሪዎች ዕውቀትን ማስገኘት መቻል አለባቸው፡፡

ተማሪዎች በይዘት ተኮር ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴ ከአከራካሪ ድርሰት የመጻፍ ክሂል አለባውያን ውስጥ ይዘትን እና በመጻፍ ክሂል ተነሳሽነት ውስጥ ደግሞ ግለብቃትን ማጎልበት የዚህ ጥናት መነሻ ከመሆኑም በላይ በትምህርት ሂደት ዋነኛ ጉዳይ ሆኖ እያለ በቀደምት አገርኛ ጥናቶች አለመዳሰሱ ርዕሰ ጉዳዩን ተመራጭ አድርጎታል፡፡ በተጨማሪም በአንደኛ ደረጃና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተገኝ አማርኛ ቋንቋን የማስተማር ልምድና ከሌሎች የቋንቋ መምህራን ጋር ኢመደበኛ በሆነ መልኩ በመወያየት የተገኘ ልምድ ብዙ ተማሪዎች ክርክራዊ ድርሰት የመጻፍ ክሂል ችግር እንዳለባቸውና የመጻፍ ክሂል ችሎታቸውን ለመመዘን በሚሰጣቸው የማጠቃለያ ፈተና ውጤታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ለመገንዘብ መቻሉም በዚህ ርዕስ ጥናት ለማካሄድ ሌላው መነሻ ሆኗል፡፡ ተማሪዎችም በመጻፍ ክሂል ትምህርት ወቅት በጽሁፍ ክሂሉ ላይ በአግባቡ ከመሳተፍ፣ ክትትል ከማድረግና በትምህርቱ ከመሳብ ይልቅ ከትምህርቱ ውጭ በሆኑ ስራዎች መጠመድ ማስተዋል ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ዝቅተኛ የሆነውና ለመጻፍ ክሂል ትምህርት ተነሳሽነት የሌላቸው ከአቀራረብ ዘዴው ጋር የተያያዘ ችግር ይሆን? የሚል ጥያቄ ስለሚያስነሳ በጉዳዩ ላይ ጥናት ለማካሄድ አነሳስቷል፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ዓላማ በይዘት ተኮር ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴ ከአከራካሪ ድርሰት የመጻፍ ክሂል አለባውያን ውስጥ ይዘትን እና በመጻፍ ክሂል ተነሳሽነት ውስጥ ደግሞ ግለብቃትን በመጻፍ ተነሳሽነት ላይ ያለውን ውጤታማነት መመርመር ይሆናል፡፡

**4. የአጠናን ዘዴ**

ይህ ጥናት ከፊል ሙከራዊ የምርምር ስልትን ተከትሎ የተከናወነ ሲሆን የሁለት ቡድን ቅድመና ድህረ ፈተና ንድፍን ተግባራዊ አድርጓል፡፡ ተላውጦችን በተመለከተ በይዘት ተኮር ቋንቋን በማስተማሪያ ዘዴ መማር ነጻ ተላውጦ ሲሆን ከአከራካሪ ድርሰት የመጻፍ ክሂል አለባውያን ውስጥ ይዘትን እና በመጻፍ ክሂል ተነሳሽነት ውስጥ ደግሞ ግለብቃት ጥገኛ ተላውጦዎች ናቸው፡፡

**4.1 የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ**

ይህ ጥናት በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ ስር በሚገኘው የዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን፣ በ!0ኛ ክፍል ብቻ የተገደበ ነው፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ውስጥ ካሉት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመቺ የንሞና ስልት ተመርጧል፡፡ አመቺ ንሞና ተግባራዊ የተደረገበትም ምክንያት የዚህ ጥናት መነሻ ሀሳብ በይዘት

ተኮር ቋንቋን በማስተማሪያ ዘዴ አከራካሪ ድርሰት የመጻፍ ክሂል አለባውያን ውስጥ ይዘትን እና በመጻፍ ክሂል ተነሳሽነት ውስጥ ደግሞ ግለ ብቃት ላይ ያለውን ውጤታማነት ለማረጋገጥ በሙከራ የሚሰራ እንደመሆኑ ለጥናቱ የሚያስፈልገውን ሰፊ ክፍለ ጊዜ ለማግኘት አመቺ የጥናት አካባቢና ትምህርት ቤት መምረጥ አስፈላጊ በመሆኑ ነው። የአመቺ ንሞና ዘዴ ለተጠኝዎች እኩል እድል የማይሰጥ ቢሆንም ጥናቱን በአግባቡ ለማካሄድ ከአስር ሳምንታት በላይ በማስፈለጉ እና ትምህርቱን በታቀደው ጊዜ ለመስጠት ፈቃደኛ የሆነ ትምህርት ቤት በማስፈለጉ የንሞና ስልቱ ተመርጧል።

በናሙናነት የተመረጡ ተማሪዎች በ2014 ዓ.ም በዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በ11 የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ተመድበው ከሚማሩት 609 /ስድስት መቶ ዘጠኝ/ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ ሲሆን በአንድ ክፍል በአማካይ 55 ተማሪዎች ይማራሉ። ይህ ጥናት በሙከራ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ሁሉንም የ10ኛ ክፍል ተማሪዎችን በጥናቱ ማሳተፍ አስቸጋሪ ነው። ከዚህ የተነሳ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎችን ቁጥር ውስን ማድረግ ተገቢ ነው። ስለሆነም አጠቃላይ የጥናቱ አካላይ የሆኑትን 11 /አስራ አንድ/ የመማሪያ ክፍሎች ዕጣ ውስጥ በማስገባት እድል ሰጪ የንሞና አመራረጥ ዘዴ የ10ኛ - C ፣10 E እና 10ኛ - H ክፍል ቡድኖችን ቅድመ የጽሁፍ ፈተና በመፈተን ተቀራራቢ ውጤት ያገኙትን 10 ኛ - C እና የ10ኛ - E -ቡድኖች በቀላል ዕጣ ንሞና ለሙከራ እና ለቁጥጥር ቡድን ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርገዋል። ዘዴው የተመረጠበትም ለተማሪዎች እኩል እድል ስለሚሰጥና የጥናቱን ውጤት አስተማማኝ እንዲሆን ስለሚያደርግ ነው።

## 4.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጥናቱን አብይ ዓላማ ከግምት ውስጥ በማስገባት አግባብነት አላቸው ተብለው የተመረጡት መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ፈተና፣ናየጽሁፍ መጠይቅ እና ምልከታ ናቸው። በዚሁ መሰረት የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑ ተማሪዎችን የመጻፍ ክሂልን የማጎልበት ችሎታ ለመለካት መርሀ ትምህርቱንና መማሪያ መጽሀፉን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና በተግባር ላይ ውሏል። ቅድመ ፈተናው የተማሪዎችን ዳራዊ ዕውቀት ለመለካት የተዘጋጀ ሲሆን ፈተናው ለጥናቱ ተሳታፊዎች ከመሰጠቱ በፊት በሁለት ሦስተኛ ዲግሪ ያላቸው የቋንቋው መምህራን እና ሌሎች የፈተና ባለሙያዎች አስተያየት እንዲሰጡበትና በጥናቱ በማይካተቱ 104 /አንድ መቶ አራት/ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሙከራ (Pilot test) ተደርጎበት ተሻሽሎ ተዘጋጅቷል። ድህረ ፈተናውም ከቅድመ ፈተናው ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ የተዘጋጀ ሲሆን በተለያየ ስልት የተማሩ ቡድኖች

የመጻፍ ክሂል ችሎታቸው ምን ያህል እንደሆነ መረጃ የሚሰጥ ነው። ይህም መርሃ ትምህርቱንና የመልመጃ ዓይነቶችን መሰረት አድርጎ ተዘጋጅቷል። ፈተናው ለተሳታፊዎች ከመሰጠቱ በፊት በሁለት የቋንቋ ምሁራን እንዲገመገሙ ተደርጎ ተሸሽሎ ተዘጋጅቷል።

ፈተናውን የማረም ሂደት በተመለከተ ለአራሚዎቹም Jacobs et al. (1981) ያስቀመጡትን የማረሚያ 85 መስፈርቶች ከቀረበላቸውና አጠር ያለ ማብራሪያ ከተሰጣቸው በኋላ የእርማቱን ሂደት ሊያከናውኑ ችለዋል። ተማሪዎቹ የተፈተኗቸውን ፈተናዎች በሶስት አራሚዎች እንዲታረሙ ከተደረገ በኋላ የአስተማማኝነት ደረጃቸው በSPSS እንዲፈተሽ ተደርጓል። ስለሆነም በቅድመ እና በድኅረ ፈተናው 0.7 በላይ እንደሆነ በክሮንባኽ አልፋ ውጤት ተመዝግቧል።የተመዘገበው ውጤት የሚያመለክተው ለቅድመም ሆነ ለድኅረ የመጻፍ ክሂል ፈተና የቀረቡት ጥያቄዎች አስተማማኝነታቸው ከፍተኛ እንደሆነ ነው።

የጽሁፍ መጠይቅ የዚህ ጥናት ሌላኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው። የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በተለያየ ይዘት ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ መማር የክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂል ትምህርትን ከመማራቸው በፊትና ከተማሩ በኋላ ያላቸውን የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት ለማነጻጸር በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት አገልግሏል። የተማሪዎቹን ቅድመ እና ድኅረ ግለ ብቃት የመጻፍ ተነሳሽነትን ለመለካት ተግባር ላይ የዋለውን የጽሑፍ መጠይቅ ለማዘጋጀት ከተነሳሽነት ጋር ሊዛመዱ የሚችሉ ስነልቦናዊ አተያዮችን ከተለያዩ ምሁራን በመውሰድ በጽሑፍ መጠይቅ መልክ እንዲዘጋጅ ተደርጓል። የመጻፍ ተነሳሽነትን ለመለካት የሚያገለግለውን ግለ ብቃትን የተመለከተውን የጽሁፍ መጠይቆች የተወሰዱት ከMills and Péron (2009) እና Payne (2012) መጠይቅ ላይ ነው።ለዚህ ጥናት በሚያመች መልኩ ተሻሽለው የተወሰዱ ሲሆን መጠይቁ ለተሳታፊ ተማሪዎች ከመሰጠቱ በፊት ሦስተኛ ዲግሪ ባላቸው ሁለት መምህራን እንዲገመገም ተደርጓል። በተጨማሪም የጽሁፍ መጠይቁን አስተማማኝነት ለመለካት የጥናቱ ተሳታፊዎች ባልሆኑ 104 /አንድ መቶ አራት/ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የቅድመ ሙከራዊ ጥናት ተካሂዶበት ተሸሽሎ ተዘጋጅቷል።

በመጠይቁ ውስጥ የተካተቱ ጥያቄዎች የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ያላቸውን የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት እንዲገልጹ በማድረግ ላይ ያተኮሩ ናቸው።የጥቄዎቹ ዓይነት ዝግ ሲሆን የLikert Scale የአጠያየቅ ስልትን በሬቲንግ ስኬል የተዘጋጁ መጠን አመልካች ጥቄዎች ናቸው። የጥቄዎቹ ብዛት 10 ነው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ

በጣም እስማማለሁ (4)፣ እስማማለሁ (3) ፣ አልስማማም (2) እና በጣም አልስማማም(1) የሚሉ አማራጮች ተሰጥተዋል፡፡

ተማሪዎቹ የሞሉትን የጽሑፍ መጠይቅ የአስተማማኝነት ደረጃውን ለማስላት ክሮንባኽ አልፋ የቀመር ስሌት ተግባር ላይ ውሏል፡፡ በዚህም መሰረት አስር ጥያቄዎችን በ SPSS ውስጥ ኮድ ሰጥቶ በማስገባት የአስተማማኝነት ደረጃው እንዲሰላ የተደረገው የጽሑፍ መጠይቅ፣ የክሮንባኽ አልፋው ጤቱ 0.7 በላይ ሆኗል፡፡ ይህም ሲተረጎም ለተማሪዎቹ የቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ አስተማማኝነቱ ከፍተኛ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡ ፡ ሦስተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የሆነው ደግሞ ምልከታ ነው፡፡ በክፍል ውስጥ የሚኖረውን የመጻፍ ክሂል ትምህርት አሰጣጥ ምን እንደሚመስል ለማየት ምልከታ ተከናውኗል፡፡ በዚህ ጥናት ስራ ላይ የዋለው የተዋቀረ (structured) የሚባለው የምልከታ ዓይነት ነው፡፡ ምክንቱም፣ በተዋቀሩ መስፈርቶች አማካይነት አጥኝው ተጨባጭ መረጃዎችን መሰብሰብ እንዲችል ረድቶታል (Tashakkori & Teddlie, 2003)፡፡

ሌላው የተዋቀረ ምልከታ አጥኝው በክፍል ውስጥ ምንም ነገር ያዳምጥ መምህሩ የሚያከናውነውን ነገር በቀጥታ እንዲመለከት የማስቻል ጠቀሜታ አለው (Robson,1993)፡፡ ስለዚህም ስራ ላይ የዋለው ምልከታ የተዋቀረ (structured) የሚባለው ዓይነት ነው፡፡ በዚህም መሰረት መምህሩ ትምህርቱን የሚያስተምረው እንዴት ነው የሚለውን በክፍል ውስጥ በመገኘት የመምህሩን እና የተማሪዎችን የመማር ማስተማር ሂደት እንዲሁም ክፍሉን አጠቃላይ ሁኔታ ለመታዘብ ተሞክሯል፡፡

ምልከታውን ለማካሄድ አስቀድሞ የመከታተያ ቅጽ (check list) ተዘጋጅቷል፡፡ መከታተያ ቅጹ በዋናነት Chen (1994) ስለውጤታማ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አሰጣጥ ምንነትና ስለሚያካትታቸው ተግባራት ከገለጹት ጽሁፍ የተዘጋጀ ነው፡፤የምልከታ መከታተያው ቅጽ የዝግ ጥያቄ መልስ መስጫ መለኪያዎች ባሉት ሊከርት ስኬል የተዘጋጀ 5 ክፍሎች ያሉትና 11 የትኩረት ነጥቦች የያዘ ነው፡፤የምልከታ መከታተያ ቅጹን ተገቢነት ለመፈተሸ ጥናቱ ከመካሄዱ በፊት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በዘርፉ የሦስተኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሉ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ በዘርፉ ሦስተኛ ዲግሪ ያለው አንድ መምህር እና በጥናቱ አማካሪዎች እንዲገመገም ተደርጓል፡፡

እነዚህ መምህራንና አማካሪዎች በሰጧቸው አስተያየቶች መሰረትም መጨመር የሚገባቸው ተጨምረው ፣ መቀነስ የሚገባቸውም ተቀንሰው፣ ግልጽነት የሚጎድላቸው ጽንሰ ሀሳቦች ግልጽ ሆነው እንደገና ተሻሽለው

ተዘጋጅተዋል። የዘርፉ ባለሙያዎች ግምገማና አስተያየት መሰረት በማድረግም የምልከታ መከታተያ ቅጹን ተገቢነት (validity) ለማረጋገጥ ጥረት ተደርጓል። በመሆኑም የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ለአስራ ስድስት ክፍለ ጊዜያት እንዲማሩ ሲደረግ፣ በዘጠኙ ክፍለ ጊዜያት ላይ ምልከታ ተካሂዷል። ይኸውም በመጀመሪያዎቹ፣ በመካከል እና በመጨረሻዎቹ ሦስት-ሦስት ክፍለ ጊዜያት ምልከታው ሊካሄድ ችሏል። የምልከታው ሂደትም በተመራማሪው ተከናውኗል።በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ ምልከታ ከተካሄደ በኋላ ከሚያስተምረው መምህር ጋር የ30 ደቂቃ ቆይታ በማካሄድ ውይይት እንዲካሄድ ተደርጓል።

## 5. የመረጃ አተናተን፣ የውጤት ትንተና ማብራሪያ

### 5.1 የመረጃ አተናተን

በጥናቱ ለመረጃ መሰብሰቢያነት በተመረጡት ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ አማካኝነት የተገኘውን መረጃ ለመተንተን ነጻ ናሙና ኤፍ-ቴስት ስታቲስቲካዊ ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል። የትንተናው ስልት መጠናዊ (quantitative ) በመሆኑ SPSS የመረጃ መተንተኛ ሶፍትዌር አገልግሎት ላይ ውሏል።

### 5.2 የውጤት ትንተና

ጥናቱ እንዲመልሳቸው የታሰቡ ጥያቄዎች በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማርያ ዘዴ ማስተማር የተማሪዎችን ከአከራካሪ ድርሰት የመጻፍ ክሂል አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ እና በመጻፍ ክሂል ተነሳሽነት ውስጥ ደግሞ ግለብቃትን ለማጎልበት ከተለምዷዊ መማር የተለየ ጉልህ አስተዋፅኦ አለው? የሚል ነው። ጥያቄውንም ለመመለስ በቅድመና በድኅረ ትምህርት ፈተና እና በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡትን መረጃዎች እንደሚከተለው ተተንትነዋል። በይዘት ተኮር ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴ የክርክራዊ ድርሰት የመጻፍ ክሂል አላባውያን ውስጥ ይዘትን እና በመጻፍ ክሂል ተነሳሽነት ውስጥ ደግሞ ግለብቃትን ለማጎልበት ከተለምዷዊ መማር የተለየ ጉልህ አስተዋፅኦ አለው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በቅድመና በድኅረ ትምህርት በተሰጡት ፈተናዎች መረጃው ተሰብስቦ በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር ተሰልቶ ተግባር ላይ ውሏል። ውጤቱም በሰንጠረዥ 1- እና በሰንጠረዥ 2 -ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 1

የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ትምህርት ክርክራዊ ድርሰት የመጻፍ ክሂል አለባውያን ውስጥ የይዘት የመጻፍ ክሂል ፈተና ውጤት በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት

| ተለዋዋጩ | የተሳታፊዎች ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ- ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን ቅድመ ትምህርት | 52 | 14.9898 | 2.37986 | 1.011 | 1,102 | .317 |
| የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ትምህርት | 52 | 15.4439 | 2.22267 | | | |

በሰንጠረዥ 1 የቀረበው የጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ ውጤት የሚያሳው በሙከራ ቡድኑና በቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ትምህርት ክርክራዊ ድርሰት የመጻፍ ክሂል አለባውያን ውስጥ በይዘት አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ስታትስቲካዊ ልዩነት አለመኖሩን ያረጋግጣል፤ (**ቲ** (1,102 =**ፒ**>0.05) የ**ፒ** ዋጋ .317 ከመቁረጫ ነጥቡ በልጦ ተገኝቷል። ይህ የሚያመለክተው በሙከራ ቡድኑና በቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ትምህርት ክርክራዊ ድርሰት አላባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት ልዩነት አለመኖሩን ነው።

ሰንጠረዥ 2

በሙከራ ቡድኑና የቁጥጥር ቡድኑ የድኅረ ትምህርት ክርክራዊ ድርሰት አላባውያን ውስጥ የይዘት የመጻፍ ክሂል ፈተና ውጤት ንጽጽር በነጻ ናሙና ኤፍ-ቴስት

| ተለዋዋጩ | የተሳታፊዎች ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ- ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን ቅድመ ትምህርት | 52 | 18.9139 | 2.97251 | 40.875 | 1,102 | .000 |
| የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ትምህርት | 52 | 15.5554 | 2.34820 | | | |

በሰንጠረዥ -2 እንደተመለከተው ምናልባትም ስህተት 5%( ፒ< 0. 05) በመተው ወይም 95% እርግጠኛ በመሆን በተሰራው ስሌት የነጻ ናሙና ፍተሻ ውጤት የሚያሳየው በሙከራ ቡድኑና በቁጥጥር ቡድኑ ድኅረ ትምህርት የክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን የመጻፍ ክሂል አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ስታትስቲካዊ ልዩነት መኖሩን ነው። (ቲ (1,102 =40.875ፒ <0.05)። ይህም የሙከራ ቡድኑና የቁጥጥር ቡድኑ

ከተለያዩ ክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ብቃት ያላቸው መሆኑን ከማሳየቱም ባሻገር የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት ክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን የመጻፍ ክሂል (18.9139) ከቁጥጥር ቡድኑ ክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂል ብቃት (15.5554) የበለጠ መሆኑን ያሳያል። የዚህም ምክንያቱ ተማሪዎቹ በይዘት ተኮር ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴ መማር ክሂላቸውን በማጎልበት ረገድ አዎንታዊ አስተዋፅኦ አበርክቶላቸው ሊሆን ይችላል። በትንተናው ውጤት መሰረትም በይዘት ተኮር ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴ መማር የተማሪዎችን ክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂል በማሳደግ ረገድ ሚና አለውን ? የሚለው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ አዎንታዊ መልስ ማግኘቱን ከመረጃው ማረጋገጥ ይቻላል።

ሁለተኛው መሰረታዊ ጥያቄ በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ መማር የተማሪዎችን የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት በማሻሻል ረገድ ከተለምዷዊ መማር የተለየ ድርሻ አለው? የሚል ነው ለዚህም የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነታቸውን የሚለካ የጽሁፍ መጠይቅ ተጠይቀዋል። የተገኘው መረጃም በነጻ ናሙና ቲ- ቴስት (Independent Samples t- test) ቀመር ተሰልቷል። ውጤቱም በሰንጠረዥ 3. ተመልክቷል።

<u>ሰንጠረዥ 3</u>

የሙከራና የቁጥጥር ቡድን የቅድመ ትምህርትየ ግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር

| ተለዋዋጭ | የተሳታፊዎች ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ- ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን ቅድመ ትምህርት | 52 | 2.6648 | .43962 | 2.855 | 1,102 | .094 |
| የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ትምህርት | 52 | 2.8014 | .38291 | | | |

ረዥ 3 መረጃ መረዳት እንደሚቻለው አማካይ ውጤቶቹ በንጽጽር ሲታዩ የሙከራው ቡድን ተማሪዎቹ በቅድመ ትምህርት የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት የጽሑፍ መጠይቅ መደበኛ ልይይት ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመ ትምህርት የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት የጽሑፍ መጠይቅ መደበኛ ልይይት ተቀራራቢ መሆኑን በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የጉልህነት ደረጃ እርግጠኛ ለመሆን የነጻ ናሙናዎች ቲ -ቴስት ተግባራዊ ሆኗል። በቁጥጥሩና በሙከራ ቡድኖች የቅድመ ትምህርት የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት የጽሑፍ መጠይቅ

አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል። መረጃው በነጻ ናሙና ቲ -ቴስት ሲሰላ ( ኤፍ (1,102) = 2.855P =.094) ከመቁረጫ ነጥብ 0. 05 በልጦ መገኘቱ በሁለቱም ቡድኖች የቅድመ ትምህርት የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት የጽሑፍ መጠይቅ አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ውጤቱ አሳይቷል።

<u>ሰንጠረዥ 4</u>

የሙከራና የቁጥጥር ቡድን የድኅረ ትምህርት የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር

| ተለዋዋጭ | የተሳታፊዎች ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ- ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን ቅድመ ትምህርት | 52 | 3.5304 | 0.58349 | 35.290 | 1 | .000 |
| የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ትምህርት | 52 | 2.9252 | .44636 | | | |

በሰንጠረዥ 4 የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው ደግሞ በነጻ ናሙና ቲ - ቴስት ተሰልቶ በሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አሳይቷል። ውጤቱ በ 1 የነጻነት ደረጃ (ቲ-35.290፣P <0.05) የ ፒ ዋጋ .000 ከመቁረጫ ነጥቡ 0.05 አንሶ ተገኝቷል። ይህም ሁለቱ ቡድኖች በተለያዩ ዘዴዎች ከተማሩ በኋላ የግለብቃት በመጻፍ ተነሳሽነታቸው ላይ ጉልህ ልዩነት እንደታየባቸው ያመላክታል። ከዚህም በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ የመማር ምርጫ ከተለመደው (ውጤት ተኮር) የመማር ምርጫ በበለጠ ሁኔታ የተማሪዎችን የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት ለማሳደግ የሚያስችል መሆኑን መረዳት ይቻላል።

በትንተናው ውጤት መሰረትም በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ መማር የተማሪዎችን የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት በማሳደግ ረገድ ሚና አለውን?" የሚለው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ አዎንታዊ መልስ ማግኘቱን ከመረጃው ማረጋገጥ ይቻላል።

የዚህ ጥናት ውጤት እንደሚያሳየው በይዘት ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ መማር ከክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂልን በማጎልበት ረገድ ጉልህ ሚና እንዳለው በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን የስታቲስቲክስ ቀመሩ (ፒ<0.05) ያሳያል። የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነታቸውንም በተመለከተ በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ መማር

ውጤታማነት እንዳለው በትንተናው የተገኘው ውጤት አመላክቷል። በዚህም በቅድመና በድኅረ ትምህርት ግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት መካከል በስታቲስቲክስ ጉልህ ልዩነት (ፒ< 0.05) ታይቷል።

በአጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በይዘት ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ መማርን በቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜያት ቢጠቀሙ የተማሪዎችን ክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂልና የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት ማጎልበት እንደሚቻል ጥናቱ ያሳያል።

## 5.3 የውጤት ማብራሪያ

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በይዘት ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ መማር የክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂልና የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት ላይ ያለው ውጤታማነት መመርመር ላይ ነበር። በመሆኑም በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ በተሰበሰቡት መረጃዎች በይዘት ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ መማር በክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂልን በማጎልበት ረገድ ያለውን ፋይዳ እንዲሁም በይዘት ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ መማር የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት ላይ ያሳየው መሻሻል መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ መረጃዎች በነጻ ናሙና ኤፍ- ቴስት ቀመር ተተንትነዋል። እነዚህን ዓላማዎች ለማረጋገጥ ጥናቱ መረጃዎችን በመተንተን ረገድ በቅድሚያ ያየው የሙከራ ቡድኑንና የቁጥጥር ቡድኑን ቅድመ ትምህርት የነበራቸውን የክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂል መለካት ነው። በዚህም መሰረት የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖቹ በክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂል ተፈትሿል። ከነጻ ናሙና ቲ- ቴስት የተገኘው ውጤት የተጠኝ ቡድኑና የቁጥጥር ቡድኑ በተመሳሳይ በክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂል ያላቸው መሆኑን በ 1,102 የነጻነት ደረጃ (ቲ = 40.875፣ፒ> 0.05) አሳይቷል። የ ፒ ዋጋ .317 ከመቁረጫ ነጥቡ በልጦ በመገኘቱ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ቅድመ ትምህርት ክርክራዊ ድርሰትአለባውያን ውስጥይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂል ልዩነት አለመኖሩ ተረጋግጧል።

ቀጥሎም የሁለቱም ቡድኖች በክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂል ድኅረ ትምህርት ልዩነት መኖሩና አለመኖሩ ተለይቷል። በዚህም መሰረት ድኅረ ትምህርት በይዘት ተኮር ቋንቋን በማስተማሪያ ዘዴ መማር ተግባራዊ ከተደረገ በኋላ በሙከራ ቡድኑና በቁጥጥር ቡድኑ ክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂል መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን የፒ ዋጋ .000 ከመቁረጫ

ነጥቡ 0.05 አንሶ፣ በ 1,102 የነጻነት ደረጃ (ቲ = 40.875፣ፒ< 0.05)አመላክቷል። ይህም በሁለቱ ቡድኖች ድህረ ትምህርት ክርክራዊ ድርሰት የመጻፍ ክሂል ጉልህ ልዩነት እንዳለ ያስረዳል። በመሆኑም በይዘት ተኮር ቋንቋን በማስተማሪያ ዘዴ መማር የተማሪዎችን ክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ መጻፍ ክሂል በማጎልበት ረገድ ያለው ውጤታማነት የጎላ መሆኑን የጥናቱ ውጤት አመላክቷል።

ይህም ውጤት Dueñas( 2004)፣ Grabe & Stoller (1997) Richards and Rodgers (2001) የጥናት ውጤቶች ጋር ተመሳሳይነት አለው። እንዲሁም Cammarata, L., & Tedick, D. J. (2012) Stryker & Leaver (1993) ሃሳብ ጋር የተስማማ ሆኖ ተገኝቷል። ዘዴው በክሂሉ ላይ አዎንታዊ ሚና እንዳለውና በዘዴውና በመጻፍ ክሂሉ መካከል ተዛምዶ አለው ካሉት ሀሳብ ጋር ተደጋጋፊነት አለው።

በሌላ በኩል በይዘት ተኮር ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴ የመማር ምርጫ ከትምህርት ውጤት ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ መኖሩን ካረጋገጡት Brown (2000) ፣ Grabe & Stoller (1997) Littlewood (1981)። በአንጻሩደግሞሁሉንምተማሪዎችማዕከልያደረገየማስተማሪያዘዴአይደለምበማለትከሚከራከሩ Lyster & Ballinger (2011)፣ Cammarata, L., & Tedick, D. J. (2012) ከደረሱበት ድምዳሜ ጋር ይቃረናል። ሆኖም እንደ Lyster & Ballinger (2011)፣ Cammarata, L., & Tedick, D. J. (2012) ድምዳሜ ቢሆን በዚህ ጥናት ተሳታፊ የሆኑት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በድኅረ ክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂል መለኪያ ፈተና ላይ ከቅድመ ፈተናው የበለጠና የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ባልቻሉ ነበር።

መደበኛ ልይይቱንም በተመለከተ ከቅድመ ትምህርቱ በክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂል ውጤት ይልቅ የድኅረ ትምህርቱ የመደበኛ ልይይት ውጤት አንሶ ተገኝቷል። ከዚህ አንጻር ተማሪዎቹ ክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂልን በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ መማራቸው የመጻፍ ክሂላቸውን እንዳሻሻለውና በተማሪዎቹ መካከልም የችሎታ መቀራረብን እንደፈጠረላቸው ያመላክታል።

በዚህ ጥናት ውጤት በክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ በመጻፍ ክሂል ላይ መሻሻል የታየው ተማሪዎች በክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂል ትምህርትን በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ በመማራቸው እንዲያነቡ የቀረበላቸው ምንባብ ሳቢና በተማሪዎች ምርጫ የቀረበ በመሆኑ ፣ይኸውም ትምህርቱን ቀላልና ግልጽ ስላደረገው አንብበ በመረዳት በግለ ገለጻና በጭምቃሳብ

አንቀፆችን በመጻፍ በአንቀጹም ውስጥ፡-ከተሰጣቸው ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተማሪዎቹ የጻፉት የይዘት መጣጣም መሻሻል ችሏል ቢባል ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

ሁለተኛው መሰረታዊ ጥያቄ የሚያነሳው በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ መማር የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት ላይ የሚያሳየው መሻሻል መኖር አለመኖሩን በተመለከተ ሲሆን በዚህም በኩል በሰንጠረዥ 3 እንደቀረበው የድኅረ ትምህርት የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት ከቅድመ ትምህርት በልጦ ታይቷል፡፡ የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት የመደበኛ ልይይቱም ከቅድመ ትምህርት ይልቅ በድኅረ ትምህርቱ አንሶ መገኘቱ ተማሪዎቹ በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ በክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂል ከመማራቸው በፊት የመጻፍ ፍላጎታቸውን ሊያነሳሱ የሚችሉ ቅድመ ሁኔታዎች እንዳልተመቻቸላቸው ያሳያል፡ ፡ አማካይ ውጤታቸውም ሲነጻጸር የድኅረ ትምህርት የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት የግለብቃት ተነሳሽነት በስታቲስቲክስ ጉልህ ልዩነት (ፒ < 0.05) አሳይቷል፡፡ በመሆኑም በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ መማር በተማሪዎች የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት ላይ ያሳየውን መሻሻል ያመላከተው የዚህ ጥናት ውጤት Brown (2000) ፣ Grabe & Stoller (1997) Littlewood (1981)፡፡ ከደረሱበት የድምዳሜ ሃሳብ ጋር ተደጋጋፊነት አለው፡፡ በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ መማር የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነትን ይጨምራል፤ የመጻፍ ክሂልን ያዳብራል በሚል የደረሱበት ድምዳሜ በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ መማር የግለብቃት የመጻፍ ክሂል ለማሳደግ ያለውን አስተዋፅኦ ያሳያል፡፡ ይህም ለተሳታፊ ተማሪዎች በማስተማሪያነት የቀረቡት አሀዶች ተማሪዎቹ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑና የግለብቃት ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ያደረጉ በመሆናቸው ነው የሚል አንድምታ ይኖረዋል፡፡

በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ውጤት በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ መማር፣ በክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂል የማጎልበትና የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት የማሳደግ ፋይዳ አለው ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህም ከቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት በስታቲስቲክስ ቀመር መሰረት በልጦ መገኘቱና የድህረ የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት ከቅድመ የግለብቃት መጻፍ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት ጉልህ ሆኖ መገኘቱ ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል፡፡ በጥቅሉ በዚህ ጥናት የተገኙ ውጤቶች ያመላከቱት በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ የመማር ምርጫን በተገቢው መንገድ ተጠቅሞ ማስተማር ክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂልንና የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነትን ከማጎልበት አንጻር ጉልህ አስተዋፅኦ የሚያበረክት መሆኑን ነው፡፡

## 6. ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳብ

### 6.1 ማጠቃለያ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ መማር በክርክራዊ ድርሰት አላባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂልና የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት በማጎልበት ረገድ ያለውን ውጤታማነት መመርመር ነው። በዚህም መሰረት ጥናቱ ምላሽ ሊሰጥባቸው ያነሳቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ መማር የተማሪዎችን የክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂል ለማሳደግ ከተለምዷዊው /ከነባሩ የመጻፍ ዘዴ የተለየ ጉልህ አስተዋፅኦ አለው? እና በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ መማር የተማሪዎችን የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነትን በማሻሻል ረገድ ከተለምዷዊው /ከነባሩ የተለየ ድርሻ አለው ? የሚሉት ናቸው ። የጥናቱ ተሳታፊዎች በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር በዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2014 ዓ.ም 10ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ሲከታተሉ ከነበሩ 609 /ስድስት መቶ ዘጠኝ/ ተማሪዎች ሲሆኑ እነዚህ ተማሪዎች በ11 /አስራ አንድ/ የመማሪያ ክፍሎች የተደለደሉ ናቸው።ከእነዚህ 11 /አስራአንድ/ የመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ቡድኖች መካከል በእድል ሰጪ ንሞና የተመረጡ የ10 ኛ - C፣ 10 ኛ- E እና የ10ኛ - H ክፍል ቡድኖችን ቅድመ የጽሁፍ ፈተና በመፈተን ተቀራራቢ ውጤት ያገኙትን 10 ኛ - C እና የ10ኛ - E -ቡድኖች በዕድል ሰጪ ንሞና ለሙከራ እና ለቁጥጥር ቡድን ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርገዋል።

በጥናቱም ዋናው የመረጃ መሰብሰቢያም ፈተና ሲሆን የክፍል ደረጃውን መርሀ ትምህርትና መማሪያ መጽሀፉን መሰረት በማድረግ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሆኗል። ተሳታፊዎችም በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ ከመማራቸው በፊት የቅድመ ትምህርት ፈተና እንዲሁም የጽሁፍ መጠይቅ በተለያዩ ባለሙያዎች ማስተካከያ ተደርጎበት በሙከራ ጥናት ተፈትሾ አስተማማኝ ሆኖ በመገኘቱ ፈተናውና የጽሁፍ መጠይቁ በቅደም ተከተል የተማሪዎችን የክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂልና የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነትን ለመለካት ተግባራዊ ሆነዋል። በአጠቃላይ በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች በገላጭና ድምዳሜያዊ ስታቲስቲክስ ተተንትነዋል።

ከዚያም ለማስተማሪያነት የተዘጋጁትን ቴክስቶችን ለአስር ሳምንታት ሲማሩ ቆይተዋል። ከትምህርቱ በኋላም ከቅድመ ትምህርቱ ፈተና ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የድኅረ ትምህርት ፈተና በመስጠት ለጥናቱ የሚፈለገው መረጃ

ተሰብስቧል። ቀጥሎም ድኅረ ግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነታቸውን ለመለካትና ለማነጻጸርም የጽሁፍ መጠይቁን ሞልተዋል። የጽሁፍ መጠይቁ አስር ጥያቄዎችን ያካተተ ሲሆን ጥያቄውም የተወሰደውከMills and Péron (2009) እና Payne (2012) መጠይቅላይነው።ለጥናቱ በሚያመች መልኩ በማሻሻል ለመጻፍ ያላቸውን የግለብቃት ተነሳሽነት እንዲለካ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ ውሏል።

በመጨረሻም ከቅድመ ትምህርት ፈተናውና የጽሁፍ መጠይቁ ጋር አቻ የሆነ የድኅረ ትምህርት ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ተግባራዊ በማድረግና ውጤቱን በመረጃነት በመመዝገብ በመጀመሪያ በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ መማር የክርክራዊ ድርሰት አላባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂልን ለማጎልበት ያለው ውጤታማነት ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ በነጻ ናሙና ኤፍ-ቴስት ተተንትኗል። በዚህም በቅድመና ድኅረ ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል በስታቲስቲክስ (ፒ < 0.05)ጉልህ ልዩነት በመታየቱ በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ መማር ክርክራዊ የመጻፍ ክሂል ችሎታን እንደሚያጎለብት ለመረዳት ተችሏል። በሁለተኛ ደረጃ የተነሳው መሰረታዊ ጥያቄ በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ መማር በተማሪዎች የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት ላይ ያለው ፋይዳ  ምንድን ነው ? የሚል ነበር ። በቅድመና ድኅረ ትምህርት የፍላጎት መረጃው መሰረት በተሳታፊዎች የቅድመና የድኅረ ትምህርት አማካዮች መካከል በስታቲስቲክስ (ፒ < 0.05)ጉልህ ልዩነት ታይቷል። በዚህም በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ መማር በተማሪዎች የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት ላይ ያሳየው መሻሻል መኖሩን ለመረዳት ተችሏል።

በአጠቃላይ የጥናቱ ትንተና ውጤት የክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂልና የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት ለማጎልበትና ለተማሪዎች የሚቀርቡት አሀዶች በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማርያ ዘዴ ለመማር በሚያስችሉ ስልቶች ቢቀርቡ የተሻለ ውጤት ሊገኝ እንደሚችል አመላክቷል። ትምህርቱም የመጻፍ ፍላጎት በሚያነሳሳ መልኩ ለተማሪዎች ቢቀርብ  ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ክሂል እና የግለብቃት የመጻፍ ተነሳሽነታቸው ሊጎለብት እንደሚችል ውጤቱ ጠቁሟል።

**6.2 መደምደሚያ**

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በይዘት ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ በአከራካሪ ድርሰት ከመጻፍ ክሂል አለባውያን ውስጥ ይዘትን እና ከተነሳሽነት መገለጫ ከሆኑት ውስጥ የግለ ብቃት የመጻፍ ተነሳሽነትን ማጎልበት ላይ ያለው አስተዋፅዖንን መመርመር ነበር፡፡ከዚህ በመነሳትም የጥናቱን ትንተና ውጤት መሰረት በማድረግ ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል፡፡

- ይዘት ተኮር ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴን በመጠቀም የመጻፍ ትምህርትን ማስተማር የተማሪዎችን ክርክራዊ ድርሰት አላባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ችሎታን በማዳበር ረገድ ሚና አለው ፤ እንዲሁም የመጻፍ ችሎታ በማሻሻል በኩል ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት በጥናቱ ግኝት መታየት በመቻሉ ስራ ላይ ቢውል የተሻለ ነው የሚል አንድምታ አለው፡፡
- በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በይዘት ተኮር ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ትምህርት እየተሰጣቸው አከራካሪ ድርሰት የመጻፍ ልምምድ ያደረጉበ ድኖች ክርክራዊ ድርሰት አላባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ በመጻፍ ችሎታቸው ከቅድመ ትምህርቱ ይልቅ ድኅረ ትምህርቱ ላይ መሻሻል ያሳዩ በመሆናቸው ይዘት ተኮር ቋንቋ የማስተማሪያ ዘዴየ ተማሪዎችን ክርክራዊ ድርሰት የመጻፍ ችሎታ በማሻሻል የራሱ አስተዋፅዖ እንዳለው የሚያሳይ በመሆኑ ስራ ላይ ቢውል የተሻለ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡
- በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አውድ ተማሪዎች በይዘት ተኮር ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴ እየተማሩ አከራካሪ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ልምምድ በማድረጋቸው በአከራካሪ ድርሰት የመጻፍ ችሎታቸው ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ችሎታቸውን አሻሽለዋል፤ ሆኖም በተለምዷዊው/ በነባሩ ማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩት ይልቅ በይዘት ተኮር ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴትምህርት የተማሩ ተማሪዎች አከራካሪ ድርሰት የመጻፍ ችሎታቸው ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ችሎታቸው ላይ መሻሻል አሳይተዋል፡፡ በመሆኑም ይዘት ተኮር ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ አከራካሪ ድርሰት ከመጻፍ ክሂል ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው መሆኑን ስለሚያሳይ ስራ ላይ ቢውል የተሻለ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡
- በተጨማሪም በአማርኛ ቋንቋት ምህርት አውድ ውስጥ ይዘት ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ተነሳሽነት ለማሻሻል ጉልህ ሚና አለው፡፡ በዚህም መሰረት፡-ተማሪዎች ለመጻፍ ትምህርት ያላቸውን ግለብቃታቸውን ከፍ እንዲል ይዘት ተኮር ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ የጎላ ድርሻ አለው፡፡

- በአጠቃላይ በዚህ ጥናት ይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ የተማሪዎችን ክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ችሎታ በማሻሻል ረገድ የበለጠ አቅም ስላለው እንዲሁም የተነሳሽነት መገለጫ ከሆኑት ውስጥ ግለ ብቃትን ስለሚያጎለብት ለተተግባሪነቱ ቦታ ቢሰጠው ከሚል መደምደሚያ ላይ መድረስ ተችሏል፡

## 6.3 የመፍትሄ ሀሳቦች

የዚህ ጥናት መሰረታዊ ጥያቄዎች ተመልሰውና ዓላማዎቹ ተፈትሸው በጥናቱ የተደረሰባቸውን መደምደሚያዎች ወይም ግኝቶች መሰረት በማድረግ የሚከተሉት የመፍትሄ ሀሳቦች ተጠቁመዋል፡፡

- በተካሄደው ከፊል ሙከራዊ ጥናትም ይዘት ተኮር የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ክርክራዊ ድርሰት አለባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ችሎታ ከመጻፍ ክሂል እና የተነሳሽነት መገለጫ ከሆኑት ውስጥ ከግለ ብቃት አንጻር ያለው ውጤታማነት ተፈትሾ የተገኘው ውጤት አበረታች ነው፡፡ውጤቱም፣ የሙከራ ቡድኑ  በይዘት ተኮር ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ትምህርት እየተሰጣቸው ድርሰት የመጻፍ ልምምድ ካደረጉ በኋላ በድኅረ ትምህርት ክርክራዊ ድርሰት አላባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ በመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤታቸው በይዘት ተኮር ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ትምህርት እየተሰጣቸው ድርሰት የመጻፍ ልምምድ ካላደረጉ ቡድኖች ድኅረትምህርት ክርክራዊ ድርሰት አላባውያን ውስጥ ይዘትን ጠብቆ የመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት አሳይቷል፡፡በመሆኑም የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል የመጻፍ ክሂል ሥርዓተ ትምህርት አዘጋጆች ይዘት ተኮር ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ እንዲካተት ቢያደርጉ፣ የመጻፍ ክሂል ሱፐር ቫይዘሮች፣ መምህራንና ተማሪዎች ስለይዘት ተኮር ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ  ስልጠና ወስደው ዘዴውን በመማር ማስተማር ሂደት ተግባራዊ የሚሆንበት ምቹ ሁኔታ በሚመለከታቸው አካላት እንዲፈጠር ማድረግ ያስፈልጋል፤
- ይዘት ተኮር ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴ በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታ ላይ ጉልህ የሆነ ልዩነት አምጥቷል፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት በአንድ የክፍል ደረጃ እና በአንድ ትምህርት ቤት ብቻ ተደረገ በመሆኑ ሁሉንም የክፍል ደረጃዎችንና ሁሉንም ትምህርት ቤቶችን ያካተተ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ሌሎች ጥናቶች ቢደረጉ፤

- በዚህ ጥናት ውጤት የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ ትምህርት እየተሰጣቸው ድርሰት የመጻፍ ልምምድ ካደረጉ በኋላ የግለ ብቃት የመጻፍ ተነሳሽነት አማካይ ውጤታቸው በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ ትምህርት እየተሰጣቸው ድርሰት የመጻፍ ልምምድ ካላደረጉ የቁጥጥር ወይም ተለምዷዊው ቡድኖች የግለ ብቃት የመጻፍ የተነሳሽነት አማካይ ውጤታቸው በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሮ ታይቷል። በዚህም በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ለመረዳት ተችሏል። ስለዚህ በይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ የሚመለከት ስልጠና ለሱፐር ቫይዘሮች፣ ለመጻፍ ክሂል መምህራን፣ለተማሪዎችና ለስርአተትምህርት / መርሀ ትምህርት አዘጋጆች የሚሰጥበትና ዘዴው ተግባራዊ የሚሆንበት ሁኔታ በሚመለከታቸው አካላት ቢመቻች፣ ተማሪዎቹ ለመጻፍ ያላቸው ተነሳሽነት ከፍ እንዲል ለማድረግ ያስችላል።
- የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች ልምምዱን ሲያካሂዱ የነበረው የመጻፍ ትምህርትን ከመጀመራቸው በፊት የሚጽፉበትን ዓላማ እና ምን ዓይነት ይዘት ያላቸውን ጽሁፎች እንደሚጽፉ እንዲወስኑ፣ የሚጽፉበት ርዕሰ ጉዳይ የተማሪዎችን ምርጫ / ፍላጎት ግምት ውስጥ ያስገባ በሆነ መንገድ እንዲዘጋጁ፣ እንዲያቅዱ፣ ከቢጤዎቻቸው ጋር እንዲወያዩ፣ ከመምህሩ ድጋፍ እንዲሰጣቸው የጥናቱ ግኝት ያሳያል። በመሆኑም ባለ ድርሻ አካላት መማሪያ መጻህፍቱን ሲያዘጋጁ ይዘት ተኮር ቋንቋን ማስተማሪ ዘዴን ቢያካትቱ።

**ዋቢ መጻሕፍት**


ሰለሞን ተሰማ። (1987)። "የቢጤ እርማት ተግባራዊነትና ውጤታማነት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ገላጭ ጥናት። "አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።

አማረ ተሸመ።(2010)" ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል እና ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለው ተጽዕኖ (በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት)" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሦስተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።

ኤፍሬም ጥሩነህ። (2110)።"የመጻፍ ክሂል ትምህርት አሰጣጥ፣ተማሪዎች ለመጻፍ ክሂል ያላቸው እይታ (perception) እና የመጻፍ ችሎታ ተዛምዶ፣ በአምስት ዩኒቨርሲቲዎች መነሻነት "አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሦስተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።

ክፍሌ ኃብተ ማርያም። (1989)። "የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ሃሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ"።አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።

ግርማ ኃይሉ። (2009)። "ትብብራዊ መማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል፣ ማህበራዊ ክሂልና የመጻፍ ተነሳሽነት ለማሳደግ ያለው ሚና።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሦስተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።

የሻረግ ጌታነህ። (2010)። "ቅርጽ ተኮር፣ ይዘት ተኮርና ቅርጽና ይዘት ተኮር የጽሁፍ ምጋቤ ምላሽ የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ የማሻሻል ሚና፤ በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት" አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ፣ ለአማርኛ ማስተማር ለሶስተኛ ዲግሪ የቀረበ (ያልታተመ)

Alamirew G/Mariam. (2005). A Study on the Perception of Writing, Writing Instruction, and Students' Writing, Performance.(PHD Dissertation). Addis Ababa: AAU. /Unpublished/.

Ariningsih, D. (2010). “The Effectiveness of Using Picture Series to Improve the Students’ Writing Skill Viewed from their Learning Motivation. Thesis submitted for Graduate degree in English Education, Sebelas Maret University.

Brinton, D., Snow, M., & Wesche, M. (1989). Content-based second language instruction. NY: Newbury House.

Brown, D. (2000). Principles of Language Learning and Teaching. New York: Addison Wesley Longman.

Brinton D. (2003). Content based Instruction. Practical English Language Teaching (PP199-224). New York .McGraw Hill.

Cammarata, L., & Tedick, D. J. (2012). (in press). Balancing content and language in instruction:The experience of immersion teachers. Mod-ern Language Journal

Chen, Y. (1994). “Effective instruction‷‟.Paper presented at the Annual Meeting of the Teachers of English to Speakers of Other Languages (28th, Baltimore, MD, March 8-12).

Dueñas, M. (2004). A description of prototype models for content-based instruction in higher education.

Elshirbinnnnni,I.I. (2013). The effect of the genre based approach to teaching writing on the EFL AL- Azhr secondary students. Writing skills and their attitudes towards writing: A level EFL. The Asia EFL.Journal Quarterly, 13(1).164-192.

Fahnestock, J. (2000). A rhetoric of argument. New York: McGraw Hill.

Finkbeiner, C. & S. Fehlin. 2002. Content-based instruction: Some lessons and implications. Finkelbeiner (ed.) Cambridge. Cambridge University Press.

Grabe. W. & Stoller, F.L. (1997). Content-based instruction: Research foundations.

Harston, M. (1982). A contemporary rhetoric. 3rd edition. Boston: Houghton Mifflin.

Hashemenejad, F. Zoghi, M. and Amini, D.. (2014). The Relationship between Self-efficacy and Writing Performance across Genders. Theory and Practice in Language Studies,Vol.4 (5).

Holman, William (2003). A Handbook to Literature (9th ed.). New Jersey: Prentice Hall. p. 193.

Hyland, K. (2003). Second Language Writing. Cambridge: Cambridge University Press.

Jacobs, H. L., Zinkgraf, S.A., Wormuth, D. R., Hartfiel, V.F., & Hughey, J. B. (1981). Testing ESL composition: A practical approach. Rowley, MA: Newbury House.

Kim, M. (n.d.). Genre based approach to teaching writing .9PP. 33-39) Retrieved from http://www. Doc database.net/details genre based – approach -to- teaching writing – miyoun – sophiq-1175075.html.

Kroll, B. (1991). Teaching writing in the ESL context. In M. Celce-Murcia (ed.).Teaching English as a second language (PP. 264-276). Boston: Heinle and Heinle.

Leki, I. (1996). L2 composing: Strategies and perceptions. In B. Leeds (ed.), Writing in a Second Language. Insights from First and Second Language Teaching and Research, 27-37. London: Longman.

Robson, C. (1993). Real worled research: Aresourses for social Scientists and practioner-researchers. Australia: Blackwell publishing.

Tashakkori, A. & Teddlie. C. (2003). Hand book of mixed methods in social and beheivoural research . Thousand Oaks, CA: SAGE.